## የመጽሐፍ ግምገማ

***የመጽሐፉ ርዕስ፤- The Inauthentic Existence and Other Essays***

***የመጽሐፉ ደራሲ፡- ቴዎድሮስ ተፈራ***

***የመጽሐፉ የሕትመት ዘመን፡- 2014 ዓ.ም***

***የመጽሐፍ ዳሰሳ አቅራቢ፡- ጥላሁን በጅቷል***

***አሳታሚ፡- በደራሲው የታተመ***

ሦስት መጻሕፍት በእንግሊዝኛ ያሳተመው ደራሲ ቴዎድሮስ ተፈራ የበኩር ሥራው ረጅም ልቦለድ *Journey of a Passion* ፣ ሁለተኛው መጽሐፉ *The Anatomy of ATP and Other Essays* ሲሰኝ ሦስተኛውና በዚህ ዳሰሳ አጭር ምልከታ ያደረግንበት ደግሞ *The Inauthentic Existence and Other Essays* ይሰኛል፡፡ ይህ ሥራ 12 ወጎችን፣ ምስጋና፣ የደራሲው ማስታወሻ እና ሙዳየ-ቃላትን በ129 ገጾቹ ይዟል፡፡

ደራሲ ቴዎድሮስ የበኩር ሥራው ዘውግ ረጅም ልቦለድ ቢሆንም፣ የቀጣዮቹ ሁለት መጻሕፍት ዘውግ ግን ወግ (*Essay)* ነው፡፡ ይህን ዘውግ የመረጠበትን ምክንያትም በሁለቱ መጻሕፍት መግቢያ (Author's Note) ላይ አብራርቶልናል፡፡ ወግ (*Essay*) ስለሚባለው የሥነጽሑፍ ዓይነት ብያኔ፣ ልዩ ባህርያትና የይዘት ትኩረት ሳይቀር ደራሲው በመጽሐፉ መግቢያ ውስጥ አብራርቷል፡፡ በዘመናዊ ሥነጽሑፍ የወግ ዘውግ ረገድ ፊታውራሪ ሊሰኝ የሚችለውን እንግሊዛዊውን አለደስ ሃክስሊን (Aldous Huxley እ.ኤ.አ. 1894-1963) በመጥቀስ ወጎች ሊኖራቸው ስለሚችለው ቅርጽና ይዘት ጭምር በመግቢያው ዳስሷል፡፡ ከዚህ አንጻር ብሎም ስለሥነጽሑፍ የሚብሰለሰልባቸው ሥራዎቹ (ለአብነት ወግ 12ን ልብ ይሏል)፣ ቴዎድሮስ አንባቢና ደራሲ ብቻ ሳይሆን፣ የሥነጽሑፍ ሐያሲዎችና መምህራን ሊያዳብሩት የሚገባውን ሙያዊ እውቀት ያካፈለበት ሥራ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ረጅም ልቦለድ መጻፍን ተወት አድርጎ ወግ (ኤሴይ) ወደመጻፍ መግባቱ አስቦበት መኾኑን በ‹ደራሲው ማስታወሻ› ላይ በግልጽ ያስቀመጠው ቴዎድሮስ፣ ይህ ሦስተኛ ሥራው ከዚህኛው በፊት እንዳሳተመውና ***The Anatomy of ATP and Other Essays*** ሲል በሰየመው መጽሐፉ እንዳደረገው፣

- እንደ አንድ ግለሰብ ስለሕይወት ያለውን ምልከታ፣
- እንደ ሥነጽሑፍ አንባቢነቱና ጸሐፊነቱ የታዛባቸውን፣

- በዚህ ዘመን እንደሚኖር እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ስለሀገሩ ማኅበረ-ፖለቲካዊ፣ -ኢኮኖሚያዊና፣ ማኅበረ-ባህላዊ ጉዳዮች የታዘባቸውን ጉዳዮች፣ እንዲሁም በዋናነት
- በሁለት ወጎች ያቀረበውና በአንድ ወቅት ከአልኮል ሱስ ለመላቀቅ በአማኑኤል ሆስፒታል ያደረገውን ከሁለት ወራት በላይ ቆይታ የሚተርክባቸው ወጎችን ይዟል፡፡

ከእነዚህ ወጎች መካከል የተወሰኑት ላይ የወፍ-በረር ቅኝት ለማድረግ ያህል፤

- ወግ 1 *Unforgettable Characters from Amanuel* እና በመጣጥፍ 2 *The Substance Ward* (***የአማኑኤል አይረሴ ገጸ-ባሕሪያት እና ከሱስ ማገገሚያው ማዕከል***) በተሰኙ በነዚህ ሁለት ወጎች ደራሲው ቴዎድሮስ በአማኑኤል ሆስፒታል ከአልኮል ሱስ ለመላቀቅ ያደረጋቸውን ቆይታዎች ይተርካል፡፡ ወጎቹ የታካሚዎችን፣ የሀኪሞችን፣ የሠራተኞችን ወዘተ ‹‹ገመና››፣ በአስቂኝና በአስገራሚ አተራረክ ያቀርባሉ፡፡ በተለይ ‹‹**አይረሴ ገጸባሕሪያት**›› ያላቸው የአማኑኤል ታካሚዎች በቀደመው ሕይወታቸው ከባንክ ሠራተኛ፣ ሸማኔ፣ ዶክተር (3 ዶክተሮች!)፣ መምህር፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪና ደላላ አንስቶ አማኑኤል ሰው ለማስታመም መጥቶ እዛው ታካሚ ሆኖ እስከቀረው እንደ ‹‹ማንችሎት›› ዓይነት ያሉ የግለሰብ ታሪኮች መሳጭ ከመሆናቸው ባሻገር በአገራችን ከአእምሮ ህመም ጋር ተያይዞ ያሉ የአመለካከት፣ የግንዛቤና አጠቃላይ የህክምና ችግሮች በማራኪ ቋንቋና ለዛ የቀረበባቸው ወጎች ናቸው፡፡
- ወግ 3 *Of Our New Culture of Exchanging Insults in Public* የተሰኘ መጣጥፍ ሲኾን ደራሲው በተለይ በቅርብ ጊዜያት በእርሱ ምልከታ እየተስፋፋ ስለመጣ የጨዋነት እጦት ያስተዋለውን ያካፈለበት ጽሑፍ ነው፡፡
- ወግ 4 *The Inauthentic Existence* ደግሞ ለመጽሐፉ ወይም ለአጠቃላይ ስብስቦቹ እንደ ስያሜ የተወሰደው ሥራ የቀረበ ሲኾን በዚህ ወግ ቴዎድሮስ ራስን ስለመመርመር፣ ስለመፈተሽ እና በዛ ሂደትም እንደ ግለሰብ ውስጣዊ የሞራል እና የመንፈሳዊ ልኬት የማድረግን አስፈላጊነት ያብራራብታል፡፡ በዚህ ወግ ‹‹**ኢንኦተንቲክ ኢግዚስተንስ**›› እንበለው ‹‹***የውሸት ኑባሬ/ኅልውና***›› የሚለውን ጽንሠ-ሀሳብ እንዲህ ሲል ይበይነዋል፤ ***‹‹የሰው ልጆች ነጻነታቸውን በሚገባ ተጠቅመው ዕጣፈንታቸውን መወሰን የማይችሉበት አኗኗር››፡፡*** እንዲሁም ሰዎች

ስለማያገባቸው፣ ስለማይመለከታቸው ስለሌሎች ሕይወት *መፈትፈት*፣ ረብ-የለሽ ወሬ (*አይድል ቻተር*)፣ ‹‹የውሸት/የማስመሰል አደባባይ›› የኾነው የማኅበራዊ ሚዲያ፣ ወዘተ ትኩረት የተሰጣቸው ፍሬ-ነገሮች ናቸው፡፡

- ወግ 5 ***The Authentic Existence As lived by Mezgebe Belay*** ከላይ በወግ 4

  ኀሳዊ ሕይወት ወይም የውሸት ኑሮ ከሚለው ሀሳብ ጋር በተቃርኖ መልክ የቀረበና ደራሲው እውነተኛ እና የውሸት ወይም የማስመሰል ሕይወትን ልዩነት በግልጽ ያስቀመጠብ ወግ ነው፡፡ ይህ ወግ በደራሲው እይታ በራሱ መንገድ በሕይወት የተጓዘ፣ የግለሰብ ነጻነቱን ለመጠቀም የሞከረ ‹‹መዝገቡ በላይ›› የተሰኘን ሰው ሕይወት ለአብነት ያቀርባል፡፡ በበፊተኛው ወግ ‹‹**ሰው ሞቱን ብቻውን እንዲጋፈጠው የምንተወው ከኾነ ስለምን ሕይወቱን በፈቀደው መንገድ እንዲኖር አንተወውም**›› የሚለውን ሀሳብ በዚህኛው ወግ በአንድ ግለሰብ ሕይወት ተሞክሮ አመካኝቶ አጠናክሮታል፡፡

- ቴዎድሮስ የነገረ-ኑባሬን ጽንሠሀሳብ በደንብ እንዲገልጹለት የጠየቃቸውን ከታች የቀረቡትን አራት ጥያቄዎችና በወግ 2 እና 3 ያካፈላቸው ጭብጦች ስንመለከት ደራሲው ስለኤክዚስቴንሻሊዝም ያለውን ጥልቅ ንባብና እውቀት መገንዘብ እንችላለን፡፡

  - How much of the life we are living is of our making? (ከሕይወታችን ምን ያህሉ የእኛው የራሳችን ሥሪት/ውጤት ነው?)
  - Are we living a life we have consciously chosen or one that is dictated by external social or familial forces? (የምንኖረው ሕይወት እኛ ይኹነኝ ብለን የመረጥነው ወይስ ከውጭ በማኅበረሰብ አለያም በቤተሰብ የተጫነብን ነው?)
  - Does the life we are living fulfill us? (እየኖርነው ያለው ሕይወት ምሉዕ ያደርገናል?)
  - Do we fee fulfilled by the life we have chosen? (በመረጥነው የሕይወት መስመር ምሉዕነት ይሰማናል?)

ከነዚህ በተጨማሪ መጽሐፉ የሚከተሉትን ወጎች ይዟል፤

- ወግ 6 *The Art of Living with Capitalism* ‹‹ከካፒታሊዝም ጋር የመኖር ብልሃት/ጥበብ››፣
- ወግ 7 *Our Intellectual Culture and Intellectuals I came across* ምሁራዊ ባህላችንና ያጋጠሙኝ ምሁራን ፣
- ወግ 8 *Why I Reject Ethnocentrism and the Ethnocentric* ጠባብ-ብሔርተኝነትንና ጠባቦችን ስለምን እንደማልቀበላቸው፣
- ወግ 9 *A Bus Trip Taken Twenty Years Ago* ከሃያ ዓመታት በፊት የተደረገ የአውቶቡስ ጉዞ፣
- ወግ 10 *A Few Things About Chat* ጥቂት ጨዋታ ስለጫት
- ወግ 11 *On the Many Benefits of Reflecting on Death Constantly* ሳይታክቱ ስለሞት የማሰላሰል አያሌ ትሩፋቶች የነገረ ህለውና ፍልስፍና ከሚያተኩርባቸው ጭብጦች አንዱ ሞት መሆኑን ያስረዳበት ወጉ ነው፡፡
- ወግ 12 *In Defense of Reading Literature* ሥነጽሑፍ የማንበብ በረከት ሲሆን

በአጠቃላይ ወጎቹ ፖለቲካ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ፍልስፍና፣ ኢኮኖሚ እና ሥነጽሑፍ ቀመስ ጭብጦችን የሚዳስሱ ሥራዎች ሲሆኑ ከላይ እንደተጠቀሰው ለመጽሐፉ የተሰጠው ርዕስ ከወጎቹ አንዱ የኾነው ***The Inauthentic Existence*** ወግ ነው፡፡ ይህ ርዕስ ቴዎድሮስ ሊተቸው የፈለገው የማኅበረሰባችን ማኅበረ-ባህላዊ ሕጸጽ ይመስላል፡፡ በነባራዊና ልማዳዊ አስተሳሰቦች፣ በአሳሪ/ቀፍዳጅ ልማዳዊ ደንቦችና ይሉኝታ የታፈነች ነፍስ በተቀደደላት ከመፍሰስ ወይም በተሄደበት ከመራመድ ውጭ ብዙም አማራጭ የላትምና የማስመሰል፣ አርቲፊሻል፣ ጎሳዊ ሕይወት ለመኖር ትገደዳለች፡፡ በመኾኑም ‹‹ያልተመረመረ ሕይወት ካልተኖረ ይቆጠራል›› (“*The unexamined life is not worth living*”) እንዲል ሶቅራጠስ፣ ቴዎድሮስም ራስን ስለመጠየቅና መመርመር ግልጽ ለማድረግ ‹‹ኦቴንቲክ›› እና ‹‹ኢንኦቴንቲክ›› ሕይወት አስመልክቶ ሁለት ወጎችን ጎን፣ ለጎን በተቃርኖ መልክ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ቴዎድሮስ ከዚህ ቀደም በነበሩት ሥራዎቹ በተለይ ***The Anatomy of ATP and Other Essays*** በተሰኘው የወጎች ስብስብ ላይ ያሳየው የግልጽነት ሀሞት (vigor for transparency) በዚህኛው ሥራውም ደግሞታል፡፡ ቴዎድሮስ አልፎ፣ አልፎ የግል ሕይወት ምልሰተ-ትውስታ፣ አንዳንዴ ደግሞ ኑዛዜ (confession) አለያም ‹‹ገመና›› መሳይ ተረኮችን በማካፈል ስም እያሳበበና እያስታመመ የማኅበረሰብን ‹‹ገመና›› መልሶ ለማኅበረሰብ የሚያካፍል ጸሐፊ መኾኑን በድጋሚ አሳይቷል፡፡

እርግጥ ነው ‹‹ኤሴይ›› (ወግ) የተሰኘውን የሥነጽሑፍ ዘውግ የመረጠውም ዘውጉ ከልቦለድ በተለየ ይህንን ለማድረግ እንደተመቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቴዎድሮስ ለአብነት በአማኑኤል ሆስፒታል ውስጥ ያሳለፈውን ወቅት እንደዋዛ በግል ማስታወሻው ከትቦ ከማለፍ አለያም የ‹‹ልቦለድ ጥሬ ዕቃ›› አድርጎ በረጅም አለያም በአጭር ልቦለድ መልክ ከማቅረብ ይልቅ አንድ ኤትኖግራፈር ወይም ፌነመኖሎጂስት ከሚያደርገው በላቀ ደረጃ ራሱ ያሳለፈውን ሕይወትና እውነት በሥነጽሑፍ ለዛ በወግ መልክ አካፍሎናል፡፡ በተጨማሪም ቴዎድሮስ ራሱ "በደራሲው ማስታወሻ" ውስጥ እንዳሰፈረልን የተወሰኑት ወጎች "the personal and autobiographical"፣ የተወሰኑት "the objective and the factual" እና ሌሎቹ ደግሞ "the abstract universal" የሆነውን የወጎች ቅርጽና ይዘት የሚያሟሉ ናቸው፡፡